
# <u>እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 11-20/2018 የነበረው</u>
# <u>የአየር ሁኔታ ግምገማ</u>

ባለፉት አስር ቀናት ወደ ሀገራችን እየገባ የነበረዉ ዕርጥበት አዘል አየር በተለይም በመጀመሪያዎቹ ስድስት ቀናት ላይ ጠንካራ እና በብዙ ቦታዎች ላይ ዝናብ እንዲኖር ከፍተኛ አስተዋፅዖ አድርጓል፡፡ በዚሁ መሰረት በሰሜን፣ በሰሜን ምስራቅ፣ በመካከለኛዉ እና በምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ እንደነበረ የተሰበሰቡ የዝናብ መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ ይሁን እንጂ ከአስሩ ቀናት አጋማሽ በኋላ የነበረዉ ዕርጥበት ከዕለት ወደ ዕለት እየተዳከመ በመምጣቱ በአብዛኛዎቹ አካባቢዎች ላይ ደረቅ፣ ፀሃያማ እና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ አመዝኖባቸዉ የተስተዋለ ሲሆን፤ በአንዳንድ የሰሜን፣ የመካከለኛዉ እና የምስራቅ የሀገሪቱ ደጋማ ስፍራዎች ላይም የሌሊት እና የማለዳዉ ቅዝቃዜ ጨምሮ ተስተዉሏል፡፡ በአጠቃላይ ባለፉት አስር ቀናት በመካከለኛዉ፣ በምስራቅ እና ደቡብ ትግራይ፣ በአማራ እና በኦሮሚያ ክልል የሚገኙ ዞኖች፣ በአፋር ክልል ዞን 03 እና በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦች እና ህዝቦች ክልል ዞኖች እንዲሁም በጋምቤላ ክልል ዞን 01 ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለዉ ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ በተጨማሪም አልፎ አልፎ ከነበረዉ ጠንካራ የደመና ክምችት በአንዳንድ ቦታዎች ላይ ከበድ መጠን ያለዉ ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ ለመጥቀስም ያህል በአርጆ 36.2፣ በሀዋሳ 42.5፣ በአይከል 32.5፣ በባቲ 46.8፣ በብላቴ 40.5፣ በቦሬ 30.4፣ በቻግኒ 31.5፣ በጭራ 32.3፣ በድሬዳዋ 35.5፣ በዳንግላ 45.3፣ በገዋኔ 60.8፣ በጊንር 80.0፣ በጎሬ 35.7፣ በሆሳና 46.6፣ በምዕራብ አባያ 46.2 እና 37.0፣ በማጀቴ 45.7፣ በፓዌ 33.8፣ በሶኮሩ 35.3፣ በወላይታ ሶዶ 54.4 እና በማጂ 31.5 በሚ.ሜ ይገኙበታል፡፡


ባለፉት አስር ቀናት የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ ቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም በምስራቅ እና ደቡብ ትግራይ፣ በሰሜንና ደቡብ ጎንደር፣ በዋግህምራ፣ በሰሜንና ደቡብ ወሎ፣ በምዕራብ እና ምስራቅ ጎጃም፣ በከማሽ፣ በሁሉም የወለጋ ዞኖች፣ በኢሉአባቦር እና ጅማ፣ በአርሲ፣ በባሌ እና በጉጂ፣ በአፋር ክልል ዞን 03፣ በምስራቅ እና በምዕራብ ሀረርጌ፣ በጋምቤላ ክልል ዞኖች ላይ፣ በቤንች ማጂ፣ በጉራጌ፣ በስልጤ፣ በሀዲያ፣ በወላይታ፣ በከፋ፣ በሸካ፣ በሲዳማ፣ በጌዴኦ እና በሰገን ህዝቦች ላይ ከ25-130 ሚ.ሜ የሚደርስ ከ4-7 ቀናት ያህል ዝናብ የነበራቸዉ ሲሆን፤ በቦረና፣ በሊበን፣ በአፍዴር፣ በሸበሌ እና በቆራሂ ጀረር ዞኖች ላይም ከ5-19 ሚ.ሜ ከ4 ላነሱ ቀናት ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 1እና 2) ፡፡

ባለፉት አስር ቀናት የዘነበው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር ሲነፃፀር በመካከለኛዉ፣ ምስራቅ እና ደቡብ ትግራይ፣ ከጥቂት የሰሜን ጎንደር ዞን በስተቀር በሁሉም የአማራ ክልል ዞኖች፣ ከጉጂ ዞን በስተቀር በሁሉም የኦሮሚያ ክልል ዞኖች ላይ፣ በሁሉም የጋምቤላ ክልል ዞኖች፣ በአፋር ክልል ዞን 02፣ 03፣ 04 እና 05፣ በከማሽ ዞን፣ በደገሃቡር፣ በፊቅ፣ በፋፈን እና በሲቲ ዞኖች፣ በጉራጌ፣ በስልጤ፣ በሀዲያ፣ በወላይታ፣ በከፋ፣ በሸካ፣ በሲዳማ፣ በጌዴኦ፣ በሰገን ህዝቦች፣ በአንዳንድ የሊበን፣ አፍዴር፣ ሸበሌ እና ቆራሂ ጀረር ዞኖች ላይ መደበኛ እና ከመደበኛ በላይ የሆነ የዝናብ ስርጭት የነበራቸዉ ሲሆን፤ የተቀሩት አካባቢዎች ላይ ከመደበኛ በታች የሆነ ዝናብ ተመዝግቧል (ካርታ 3) ።


ካርታ1   እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 11 እስከ 20/2018 ድረስ የነበረው
የዝናብ መጠን በሚ.ሜ



ካርታ2   እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 11 እስከ 20/2018 ድረስ ዝናብ
የዘነበባቸው ቀናት ብዛት




ካርታ3 እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 11 እስከ 20/2018 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር



# እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 11- 20/2018 የነበረው የአየር ሁኔታ በእርሻው ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተጽዕኖ

ባሳለፍነው የኖቨምበር ሁለተኛው አስር ቀናት ወቅቱን ያልጠበቀ እርጥበታማ ሁኔታ በተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች ተጠናክሮ እንደነበረ የተተነተኑ መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ በተለይም በመጀመሪያዎቹ ስድስት ቀናት በመደበኛ ሁኔታ ደረቃማ የአየር ሁኔታ በሚስተዋልባቸው በሰሜን፣ በሰሜን ምስራቅ፣ በመካከለኛዉ እና በምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ወቅቱን ያልጠበቀ የተጠናከረ እርጥበት እንደነበረ መረዳት ተችሏል፡፡ ይህም የነበረው ወቅቱን ያልጠበቀ እርጥበት የእድገት ደረጃቸውን ጨርሰው ለሚገኙ የመኸር ሰብሎች የሰብል ስብሰባና ድህረ ሰብል ስብሰባ እየተከናወነ በሚገኝባቸው አካባቢዎች ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ነበረው። በአንጻሩ የተገኘው እርጥበት በተለያየ ምክንያት ዘግይተው ለተዘሩና ገና ላልደረሱ ፍሬ በመሙላት ላይ ለነበሩ የመኸር ሰብሎችና በአነስተኛ እርጥበት በነሃሴ መጨረሻ ላይ ለተዘሩ እንደ ሽንብራና ጓያ ለመሳሰሉት የጥራጥሬ እህሎችና ለቋሚ ተክሎች የውሀ ፍላጎት መሟላትና በአካባቢው ለሚገኙ አርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደሮች ለግጦሽ ሣር ልምላሜና ለመጠጥ ውሃ አቅርቦት የጎላ ጠቀሜታ ቢኖረውም፤ የነበረው እርጥበታማ ሁኔታ ለአንዳንድ የሰብል ተባዮችና በሽታዎች መከሰት ምቹ ሁኔታ እንደሚፈጠር ነው፡፡ በአንፃሩ ከአስሩ ቀናት አጋማሽ በኋላ እርጥበታማው ሁኔታ ከዕለት ወደ ዕለት እየተዳከመ በመምጣቱ ደረቅ፣ ፀሃያማ እና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ አመዝኖባቸዉ የተስተዋለ በመሆኑ ለሰብል ስብሰባና ድህረ ሰብል ስብሰባ በጎ ጎን ነበረው፡፡ በሌላ በኩል ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው ለሆኑት ለደቡብና ለደቡብ ምሥራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች የተገኘው እርጥበት ለግጦሽ ሣር ልምላሜና ለመጠጥ ውሃ አቅርቦት መሻሻል እንዲሁም በደጋማው አካባቢው ለሚካሄደው የእርሻ ስራ እንቅስቃሴ ጠቀሜታ ነበረው ካርታ 4)፡፡


ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 11 እስከ 20/2018 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



## እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 11- 20/2018 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተጽዕኖ

እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 11-20/2018 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ የነበረው ገፅታ በተመለከተ በሀገሪቱ በጥቂት የሰሜን፣ የደቡብ ምዕራብ እና የደቡብ ምስራቅ ተፋሰሶች ላይ ከከፍተኛ እሰከ መጠነኛ እርጥበት ከመስተዋሉ በስተቀር በአብዛኛዎቹ ተፋሰሶች ላይ ከፊል ደረቅ እና ደረቅ ሁኔታ አመዝኖ ተስተዉሏል፡፡ ይህንን ተከትሎ በጥቂት የታችኛውና መካከለኛው ኦሞጊቤ፣ የመካከለኛውና የላይኛው ስምጥሸለቆ፣ ገናሌዳዋ፣ መካከለኛ ዋቢሸበሌ፣ በጥቂት የአባይ እና የባሮአኮቦ ምስራቃዊው ክፍል ተዋሳኝ ተፋሰሶች ላይ ከከፍተኛ እስከ መጠነኛ የእርጥበት ሁኔታ የተገኘ ሲሆን፤ በጥቂት የታችኛው ገናሌዳዋ፣ የላይኛው ተከዜና ስምጥሸለቆ፣ የታችኛውና የላይኛው አዋሽና ባሮኦኮቦ አዋሳኝ ከፍተኛ ቦታዎች፣ በጥቂት ዋቢሸበሌ ምስራቃዊው ክፍል እንዲሁም በአብዛኛው አባይ ተፋሰሶች ላይ ከፊል ደረቅ ሁኔታ ተስተውሏል፡፡ በተቀሩት የሀገሪቱ ተፋሰሶች ላይ የበጋው ፀሃያማ፣ ነፋሻማና ደረቅ የአየር ሁኔታ አመዝኖ ነበር (ካርታ 5) ፡፡

ካርታ 5. እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 11- 20/2018 በተፋሰሶች ላይ የነበረው የእርጥበት መጠን



## <u>እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 21-30/2018 የሚኖረው</u>

## <u>*የአየር ሁኔታ አዝማሚያ*</u>

*በመደበኛ ሁኔታ በኖቬምበር የመጨረሻዎቹ አስር ቀናት በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የበጋዉ ደረቅ፣ ፀሃያማ እና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ አመዝኖባቸዉ ይቆያል፡፡ በተጨማሪም በአንዳንድ በሰሜን ምስራቅ፣ በመካከለኛዉ፣ በምስረቅ እና በደቡብ ደጋማ ቦታዎች ላይ አልፎ አልፎ የሌሊት እና የማለዳዉ ቅዝቃዜ የመጠናከር እና በጥቂት ስፍራዎች ላይም ዉርጭ የማስከተል አቅም ይኖረዋል፡፡*

*በሚቀጥሉት አስር ቀናትም በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የበጋዉ ደረቅ፣ ፀሃያማ እና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ አመዝኖባቸዉ እንደሚቆይ ይጠበቃል፡፡ በሌላ በኩል አልፎ አልፎ አነስተኛ እርጥበት አዘል አየር ወደ ደቡብ አጋማሽ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ እንደሚገባ የትንበያ መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘም በዚህ ወቅት ዝናብ በሚጠበቅባቸዉ በደቡብ እና በደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የሚኖረዉ ዝናብ አነስተኛ መጠን ያለዉ እንደሚሆን ይጠበቃል፡፡ በተጨማሪም አልፎ አልፎ ከሚኖራቸዉ የደመና ሽፋን የሰሜን ምስራቅ፣ የመካከለኛዉ እና የምስራቅ የሀገራችን አካባቢዎች በጥቂት ስፍራዎቻቸዉ ላይ አነስተኛ መጠን ያለዉ ዝናብ የማግኘት ዕድል ይኖራቸዋል፡፡*

<u>*በዚሁ መሰረት በመጪዎቹ አስር ቀናት በጉጂ፣ በቦረና፣ በሊበን፣ በአፍዴር፣ በደቡብ ኦሞ፣ ሰገን ህዝቦች እና በባሌ ቆላማ ስፍራዎች ላይ መደበኛ የሆነ ዝናብ የሚጠበቅ ሲሆን፤ በምስራቅ እና ደቡብ ትግራይ፣ በሰሜን እና ደቡብ ወሎ፣ በሰሜን ሸዋ፣ በአርሲ እና ባሌ ደጋማ ስፍራዎች፣ በምስራቅ እና በምዕራብ ሀረርጌ፣ በሲዳማ፣ በፋፈን እና በሲቲ እንዲሁም በጅማ እና ኢሉአባቦራ ዞኖች ላይ አነስተኛ መጠን ያለዉ ዝናብ ሊኖራቸዉ እንደሚችል የትንበያ መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ የተቀሩት የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ደረቅ፣ ፀሃያማ እና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ አመዝኖባቸዉ እንደሚቆይ ይጠበቃል፡፡ በተጨማሪም የሌሊት እና የማለዳዉ ቅዝቃዜ በአንዳንድ የሀገሪቱ ደጋማ ስፍራዎች ላይ ከሞላ ጎደል ቀጣይነት እንደሚኖረዉ ይጠበቃል፡፡*</u>

## <u>እ.ኤ.አ. ከኖቬምበር 21-30/2018 የሚኖረው የአየር ሁኔታ</u>

## <u>በእርሻው ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተጽዕኖ</u>

በመደበኛ ሁኔታ በኖቬምበር ሶስተኛው አስር ቀናት በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ደረቃማ የእርጥበት ሁኔታ የሚስተዋል ሲሆን፤ በሌላ መልኩ በደቡብ ምዕራብ፣ በደቡብና በደቡብ ምስራቅ እንዲሁም በመካከለኛው አካባቢዎች ላይ መጠነኛ የሆነ እርጥበት የሚያገኙበት

ጊዜ ነው፡፡ በተሰጠው የአየር ሁኔታ ትንበያ መሠረት በሚቀጥሉት የኖቬምበር ሶስተኛው አስር ቀናት በአብዛኛው የበጋው ደረቃማው የእርጥበት ሁኔታ እንደሚያመዝን በትንበያው ተመልክቷል፡፡ ደረቃማው የእርጥበት ሁኔታ በተለይም የመኸር ሰብል ለሚሰበስቡና የድህረ ሰብል ስብሰባ ተግባራትን ለሚያከናውኑ አካባቢዎች አዎንታዊ ሚና ይኖረዋል፡፡ እንዲሁም የሰሜን ምስራቅ፣ የመካከለኛዉ እና የምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች በጥቂት ስፍራዎቻቸዉ ላይ አነስተኛ መጠን ያለው ዝናብ የማግኘት ዕድል ስለሚኖራቸው በሰብል ስብሰባና ድህረ ስብሰባ ላይ በተወሰኑ ቦታዎች ላይ አሉታዊ ተጽእኖ እንደሚኖረው ይጠበቃል፡፡ በመሆኑም አርሶ አደሮች በየጣልቃው የሚኖረውን ምቹ ሁኔታ ከግምት በማስገባት የደረሱ ሰብሎችን በአግባቡና በጊዜው እንዲሰበስቡ ይመከራሉ፡፡ በሌላ በኩል በዚህ ወቅት ዝናብ በሚጠበቅባቸዉ በደቡብ እና በደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ አነስተኛ መጠን ያለዉ እርጥበት እንደሚኖራቸው ይጠበቃል፡፡ ይህም የሚጠበቀው መጠነኛ እርጥበት በተለያየ እድገት ላይ ለሚገኙ የበጋ ወቅት ሰብሎች፣ ለቋሚ ተክሎች እንዲሁም ለግጦሽ ሳርና ለመጠጥ ውሀ አቅርቦት በጎ ሚና ይኖረዋል፡፡

## እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 21-30/2018 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በውሃው ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት አስር ቀናት ውስጥ የበጋው ፀሐያማ፣ ነፋሻማና ደረቅ የአየር ሁኔታ በአብዛኛዎቹ የአገሪቱ ተፋሰሶች ላይ የሚያመዝን ቢሆንም፤ በደቡብ፣ ደቡብ ምስራቅ፣ በጥቂት የሰሜን ምስራቅ፣ የመካከለኛዉ እና የምስራቅ የሀገሪቱ ክፍል ተፋሰሶች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ ሊኖር እንደሚችል ትንበያው ይጠቁማል፡ በዚህ መሰረት የአባይ ደቡባዊውና ምስራቀዊው ክፍል፣ የላይኛው ባሮአኮቦ፣ የላይኛውና መካከለኛው ዋቢሸበሌ፣ አብዛኛው ኦሞጊቤ፣ የታችኛው ስምጥሸለቆ፣ አብዛኛው ገናሌዳዋ እንዲሁም የመካከለኛው አዋሽ አዋሳኝ የሆኑት ከፍተኛ ቦታዎች እና ጥቂት የላይኛው ተከዜ ተፋሰሶች ላይ አነሰተኛ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚያገኙ ይጠበቃል፡ በእነዚህ ተፋሰሶች ላይ የሚገኘው እርጥበትና የደመና ሽፋን በበጋ ወቅት የሚኖረውን የትነት መጠን በማረጋጋት አስተዋፅዖ ከማድረጉም በላይ የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም የተገኘውን ዝናብ በመሰብሰብ ለውሃ ፍጆታ ተጨማሪ ግብዓት እንዲሆን ማድረግ ይቻላል፡